# የእነከድጃ ግቢ

18-30ኛው ሳምንት

2ኛ ክፍል

መጽሐፍ 15



# የእነከድጃ ግቢ

መጽሐፍ 15 | 2ኛ ክፍል | 18-30ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



የእነከድጃ እናትና አባት
እጅግ ደስ የሚል ቤት
ሠርተዋል።

ቤቱ ብቻ ሳይሆን ግቢውም
በጣም ያምራል:: ይህም ግቢ
እንዲያምር ካደረጉት መካከል
ከድጃ አንዷ ናት:: ከድጃ
በግቢው ውስጥ ያሉትን
አትክልቶች ትኮተኩታለች፤
ውሃ ታጠጣለች:: ሌሎች
የቤተሰብ አባላትም ያግዟታል::



የእነከድጃ ግቢ የተለያዩ
አበባዎች ተተክለውበታል።

አበባዎቹ በጣም ያምራሉ:: አበባዎቹ የተለያዩ ቀለማት አሏቸው:: የቀለማቱ መለያየት ተመልካችን ያስደስታል:: ሲመለከቷቸው ቢውሉ አይሰለቹም:: በነጭ አበባዎቹ መካከል አልፎው አልፎው የሚታዩት ጽጌሬዳዎች ልዩ ውበት አላቸው::



ጽጌሬዳዎቹ ሽታቸው ከሩቅ ያውዳል።



የእነከድጃ ግቢ በሳር የተሸፈነ ነው። ሳሩ የተተከለው ከቤቱ ፊትለፊት ባለው ሰፊ ቦታ ላይ ነው።

ሳሩ በየቀኑ ውሃ ስለሚጠጣ ለምለምና አረንጓዴ ነው፡፡ በአጭር በአጭሩ ይታጨዳል፡፡ ሳሩ ግቢውን በጣም አሳምሮታል፡፡

ከላዩ ላይ አረፍ ሲሉበት በጣም ይመቻል። በእንክድጃ ግቢ ውስጥ በአለው የሳርና የአበባ ተክል መካከል ጥዶች ተተክለዋል።

ጥዶቹ አረንጓዴ ቀለም
አላቸው:: ጥዶቹ የተተከሉት
ቀጥ ባለ መስመር ነው::
ተሰልፈው የቆሙ ይመስላሉ::
በየጊዜው ስለሚከረከሙ
አጫጭርና ሰፋ ሰፋ ያሉ
ናቸው:: የነከድጃ ግቢ
ያስደስታል::

USAID

ከአሜሪካን ህዝብ